Ayalew Bitane and Associates Law Office 0911911313

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 232474
ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ አሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- አቶ አንዋር ከድር ሁሴን - ጠበቃ ጣሰው ማሞ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጆን ብስኩት እና ጓደኞቻቸዉ የጋራዥ አገልግሎት ኅብረት/ሽ/ማኅበር - ጠበቃ ዘሪሁን አዳሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመኖሪያ ቤት አካባቢ በሚሰራ የጋራዥ ሥራ ተፈጥሯል የተባለዉን የድምጽና የኬሚካል ብክለት ለማስወገድ የቀረበ ክስ በሚመለከት በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች እና የስር 2ኛ ከሳሽ ወ/ሮ ናጂያ ናስር ረሺድ በአሁን ተጠሪ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ በመሰረቱት ክስ ሲሆን የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ሥራ ዕድል ፈጠራ እና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ ተከራክሯል፡፡ አመልካች አሻሽለዉ በመሰረቱት ክስ ተጠሪ ምንም ዓይነት ፍቃድ ሳይኖረዉ በመንደር ዉስጥ የመኪና ማደሻ ጋራዥ በመክፈት የመተላለፊያ መንገድ በመዝጋት የመኪና ቀለም ሲቀባም የሚወጣዉ ኬሚካል በጤናችን ላይ ችግር እየፈጠረብን ይገኛል፡፡ እንዲሁም የመኪና አካል በሚሰሩበት ወቅት የሚወጣዉ ከፍተኛ ድምፅ በስላማዊ ህይወታችን ላይ የመንቀሳቀስ እና የጤና ችግር ፈጥሮብናል፡፡የስር 2ኛ ተከሳሽ ለችግራችን መፍትሄ እንዲሰጠን ጠይቀን ፍቃደኛ አልሆነም፡፡በመሆኑም ይህ ድርጊት የሁከት ተግባር በመሆኑ የሁከት ተግባሩ እንዲወገድልን እና ቦታዉ ለጋራ[illegible] ማይሆን ቦታዉን እንዲለቁልን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

CamScanner

ተጠሪ በሰጠዉ መልስ አመለካች ይዞታዉን በእዉነት የሚያዙበት ባለመሆኑ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም። የአመልካች ይዞታ ቀደም ብሎ ተጠሪ የጋራዥ ሥራዉን ከሚሰራበት ቦታ በእጅጉ የራቀ የቀበሌ ቤት የነበረ ሲሆን አመልካች መንግስት ከሰጣቸዉ ይዞታ በላይ በግምት 300 ካ/ሜትር የሚሆን ይዞታ በወቅቱ ያለዉን አገራዊ ሁኔታ በመጠቀም የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ትኩረታቸዉን ወደሀገራዊ ጉዳይ አዙረዋል በማለት የተጠቀሰዉን ቦታ በሕገ-ወጥ መልኩ ወረዉ አጥረዉ የያዙትን ይዞታ መሰረት አድርገዉ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ በሕገ-ወጥ መልኩ በያዙት እና መብት በሌላቸዉ ይዞታ ላይ ተመስርተዉ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ አይችሉም። ተጠሪ የጋራጅ አገልግሎት አየሰጠ የሚገኝበትን ቦታ አስፈላጊዉን መስፈርት በማሟላት በ2012 ከመንግስት 200 ካ/ሜትር ተሰጥቶት ሕጋዊ ፍቃድ አዉጥቶ እየሰራ ይገኛል። አመልካች በጋራጅ ስራዉ ምክንያት የመተላለፊያ መንገድ አጣን በማለት በክሱ የገለጹት ሀሰት ነዉ።ቦታዉ በእንደዚህ አይነት ለተደራጁ ማህበራት መስሪያ ቦታነት ለ18 ማህበራት ተሰጥቶ ስራቸዉን የሚያከናዉኑበት ቦታ ነዉ። ለዚህ አላማ የተለየ ስፍራ ስለሆነ ክሳቸዉ ላይ የመኪና ቀለም በሚቀባት ወቅት የሚወጣዉ ኬሚካል በጤናችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ነዉ ያሉት በሕጋዊ ማስረጃ ያልተደገፈ ነዉ። ክክሳቸዉ ጋር አያይዘዉ ያቀረቡት ማስረጃ ትርጉም ተዛብቶ የቀረበ ነዉ።የሀኪም ማስረጃ ክሱ ከተሻሻለ በኋላሆነ ተብሎ ለክሱ አላማ የተዘጋጀ ነዉ። መንገድ እንደተዘጋ ለማሳየት ያቀረቡት የፎቶግራፍ ማስረጃ ከጋራዡ ግቢ ዉስጥ የተወሰደ ነዉ።አመልካች ክሱን ያቀረቡት ለጋራዥ ሥራ የተሰጠንን ቦታ ለራሳቸዉ ለመጠቀም ካላቸዉ ሀሳብ በመሆኑ ክሱ የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የለዉም ተብሎ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል።

የሥር 2ኛ ተከሳሽ በሌለበት እንደታየ መዝገቡ የሚያሳይ ሲሆን ጣልቃ ገብ በሰጠዉ መልስ ተጠሪ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታዎች አሰጣጥ፣አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ መሰረት የተደራጀና ወደሥራ የገባ እንደሆነ፣የጋራዥ ሥራ እየሰራ የሚገኘዉም ለዚሁ ሥራ በፈቀደለት መስሪያ ቦታ ብቻ እንደሆነ፣የዘጋዉ መላለፊያ መንገድ እንደሌለ፣ሥራዉ የጤና አክል ሊፈጥር የማይችልና የክሱተ የጠና አክልም የለም በማለት ተጠሪን በመደገፍ ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 045603 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና የተለያዩ ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 09/09/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአመልካች ምስክሮች የአመልካች ቤቱሰቦችና ተከራይ ሲሆኑ መሰረታዊ ልዩነት በሌለዉ ሁኔታ እንደክሱ ያስረዱ ቢሆንም የምስክርነት ቃላቸዉ ተአማንነት ያለዉ አይደለም።በአንጻሩ የተጠሪ ምስክሮች ዘመድ ያልሆኑና የአመልካችን ክስ በሚያስተባብል አኳኋን ከጋራዡ የሚወጣ ድምጽ የድምጽ ብክለት ያስከትላል የሚባል እንዳልሆነና የመተላለፊያ መንገድም እንዳልተዘጋ መስክረዋል።ከሁሉ በላይ በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ ሀኪሞች ቦርድ፣ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣የመድሐኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን እና ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላን እና ልማት ኮሚሽን የመጡ ሙያዊ አስተያየቶች ስንመለከት በቦታዉ የጋራዥ ሥራ እንዲሰራ ሊፈቅድ እንደሚቻል፣ተጠሪ ሥራዉን ለመስራት ፈቃድ እንዳለዉ ፣የአመልካች ልጅ በሽታዉ ከቀለም ጋር ባይያያዝም ከጋራዡ የሚወጡ ኬሚካሎች የጤና ጉዳት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በመረጋገጡ አመልካች ጋራዡ ይነሳልኝ/የሁከት ተግባሩን ያቁሙልን በማለት ያቀረበዉን ክስ በክፊል በመቀበል አመልካች ከጋራዡ ዉስጥ የሚሰራዉን የመኪና ቀለም መቀባት ሥራ በሰዎች ወይም በአመልካች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል በመረጋገጡ ድርጊቱ የሁከት ተግባር በመሆኑ ተጠሪ ሊያቆም ይገባል።አመልካች ቤቱን ከመንግስት መከራየታቸዉ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከማቅረብ የሚከለክላቸዉ አይደለም።ስለሆነም ተጠሪ በጋራዡ ዉስጥ የሚሰራዉን የመኪና ቀለም መቀባት ሥራ በሰዎች ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል በመረጋገጡ የሁከት ተግባር ስለሆነ ሁከቱ ይወገድ በማለት ወስኗል።

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ [illegible] ቤቱ በመ/ቁጥር 36650 ላይ በቀን 14/10/2014ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በዓ/ህ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር

CamScanner

337 መሰረት ሰርዝባቸዋል።በመቀጠል ለከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸዉን ያቀረቡ ቢሆንም በመ/ቁጥር 36839 ላይ በቀን 13/11/2014ዓ/ም በተሰጠ ትእዛዝ አቤቱታዉ ተሰርዝባቸዋል።

አመልካች በቀን 04/12/2014ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ የጋራዥ ሥራ እየሰራ ያለዉ ባልተፈቀደለት በአመልካች መኖሪያ ቤት በር ላይ ነዉ።ይህም የአመልካችና መዉጫ መግቢያ ከማጥበቡም በላይ ከቀለም ቅቡ ሌላ መኪና ለማደስ የሚጠቀመዉ የኦኪስጂን ጢስ እና መኪና ሲቀጠቀጥ የሚወጣዉ ብናኝ ወደ አመልካች ቤት ስለሚገባ በታማሚዉ ልጅ ላይ ዘላቂ ችግር እንደሚያስከትል የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይመለከቱ የቀለም መቀባቱ ሥራ ብቻ እንዲቆም መወሰናቸዉ ከተፈቀደለት ቦታ ዉጭ ያለፈቃድ እንዲሰራ የሚያበረታታና ሕጋዊ ሽፋን የሚሰጥ ስህተት ነዉ።የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር በስፍራዉ በመገኘት እንዳረጋገጠዉ ጋራዥ ሥራ እየተሰራ ያለዉ ከአመልካች መኖሪያ ቤት ፊት ለፊት በ7 ሜትር ርቀት ላይ መሆኑን ሥራዉም የሚሰራዉ በተከለለ ቦታ ላይ አለመሆኑ፣የቀለም ኬሚካል በሰዉ መተንፈሻ አካላትና የቆዳ ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሆኑን አረጋግጦ እያለ፣ እንዲሁም በታማሚዉ ልጅ ላይ ጉዳት የሚያደርሰዉ የቀለም መቀባት ሥራ ብቻ ሳይሆን መኪና ለማቃናት የሚጠቀምበትን አኪስጂን እንዲሁም መኪና ሲቀጠቀጥ የሚወጣዉ ብናኝ ጭምር ሆኖ እያለ የጋራዥ ሥራዉ እንዲቀጥል የሚያደርግ ዉሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ የጋራዥ ሥራ የሚሰራዉ በተከለለ ቦታ እንዳልሆነ፣ቦታዉ ለጋራዥ ሥራ ሲሰጥ ለጋራዥ ሥራ አመቺ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠ ቦታ ሆኖ እያለ የቀለም ሥራ ብቻ እንዳይሰራ በሚል የተሰጠዉ ዉሳኔ ከቀለም ቅብ ሌላ በጋራዥ ለሚሰራዉ ሌላ ሥራ ኬሚካል የሚጠቀም ስለመሆን ስለመረጋገጥ አለመረጋገጡ ተመርምሮ ያለመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 07/04/2015 የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- በተያዘው ጉዳይ ላይ የአመልካች ቅሬታ ከማስረጃ ጋር የተያያዘ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጥሯል በሚል የቀረበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለዉም።ተጠሪ የጋራዥ ሥራ እየሰራ የሚገኝበት ቦታ በተለየ መልኩ በሚባል ደረጃ መሰል ሥራ ለሚሰሩ በማህበራት ተለይቶ የተሰጠ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ የተወሰነ ነዉ።ተጠሪ ሕጋዊ ፈቃድ አዉጥቶ በተፈቀደለት ቦታ እየሰራ የሚገኝ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ነዉ። አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን አዲስ ክርክር ለዚህ ሰበር ሰሚች ችሎት ስላቀረቡ ክርክራቸዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል።አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከማቅረባቸዉ በፊት ይዞታውን በአውነት የሚያዙበት እና ባልተጭበረበረ ወይም በሕጋዊ መንገድ ያገኙት መሆኑን ማስረዳት ይኖርባቸዋል።ነገር አመልካች ይዞታዉን በሕገ-ወጥ መንገድ ወደማህበራት ይዞታ በመጠጋት አስፋፍተዉ የያዙት ነዉ።የሐኪም ማስረጃ የሚያሳየዉ የአመልካች ልጅ ህመም የምጥል በሽታ እንጂ ከቀለም ቅብ ጋር የተያያዘ አይደለም። የመውጫ መግቢያ መንገድ አሳጥቶኛል ያሉትንም በማስረጃ ባለማስረዳታቸዉ ዉድቅ የተደረገ ነዉ በማለት ተከራክሯል። አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል።

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤት የአመልካች ጸኝነት ጥያቄ በከፊል ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደመረመርነዉም አመልካች በአሁን ተጠሪና በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በመሰረቱት ክስ ተጠሪ ምንም ዓይነት ፍቃድ ሳይኖረዉ በመንደር ዉስጥ የመኪና ማደሻ ጋራጅ በመክፈት የመተላለፊያ መንገድ በመዝጋት የመኪና ቀለም ሲቀባም የሚወጣዉ ኬሚካል በጤናቸዉ ላይ ችግር እንደፈጠረባቸዉ፣ እን[illegible] በመኪና አካል በሚሰራበት ወቅት የሚወጣዉ ከፍተኛ ድምፅ በሰላማዊ ህይወታቸዉ ላይ [illegible]ሳቀስ እና የጤና

CamScanner

ችግር እንደፈጠረባቸዉ ገልጸዉ እነዚህ ድርጊቶች የሁከት ተግባር ስለሆኑ ሁከቱ እንዲወገድና ቦታዉ ለጋራዥ ስለማይሆን ተጠሪ ቦታዉን እንዲለቅ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል።ተጠሪ የጋራዥ ሥራዉን የሚሰራዉ የንግድ ፈቃድ አዉጥቶ መንግስት በሰጠዉ ቦታ ላይ መሆኑን ገልጾ የቀረበበትን ክስ ክዶ ተከራክሯል።የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል እና ከተለያዩ አካላት በትእዛዝ የስቀረባቸዉን ማስረጃዎች መርምሮ ተጠሪ የጋራዥ ሥራዉን ለመስራት ፈቃድ እንዳለዉ፣ተጠሪ በጋራዡ ከሚሰራቸዉ ሥራዎች ዉስጥ የመኪና ቀለም ቅብ ሥራ በሰዎች ወይም በአመልካች ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ስለተረጋገጠ ይህ ድርጊት የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል በማለት ወስኗል።

በፍትሐ ብሔር ሕግ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሚመለከቱ የተለያዩ ደንቦች መካከል አንዱ በቁጥር 1225 ስር የተደነገገዉ በባለሀብትነት መብት አለመጠን መገልገልን የሚከለክለዉ ደንብ ነዉ።በዚህ ደንብ መሰረት ባለሀብቱ በመብቱ በሚገለገልበት ጊዜ የጎረቤቱ ሀብት ጥቅም የሚቀንስበትን ወይም የሚጎዳበትን ማናቸዉንም ከመጠን ያለፈ ነገር ከመስራት መጠበቅ እንደላበት በተለይም ጪስን ወይም ጠለሸትን ወይም በጉርብትና አኗኗር ሊታገሱት ከሚቻለዉ በላይ የሆኑትን ሽታዎች፣ ጩኸቶች ወይም ንዉጽዉጽታዎች(Nuisances) ወደ ጎረቤት እንዲሄድ ማድረግ የተከለከለ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1225(1 እና 2) ተደንግጓል። ባለሀብቱ መብቱን ከመጠን በላይ ተጠቅሟል ወይም አልተጠቀመም የሚለዉ የሚወሰነዉ የአካባቢዉን ነበራዊ ሁኔታ ወይም ልማድ በመከተልና የመሬቱን አቀማመጥና የተፈጥሮዉን አይነት በመመልከት (local custom, the position of the lands and the nature thereof) እንደሆነና ባለሀብቱ በመብቱ ከመጠን በላይ በመገልገሉ ምክንያት ጉዳት ከደረሰ ወይም ጉዳት እንደሚደረስ የሚያሲጋ ሆኖ ከተገኘ ተጎጂዉ ለደረሰበት ጉዳት ኪሳራ መጠየቅ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳት የደረሰበት ነገር ወደ ነበረበት እንዲመለስለት የመጠየቅ ወይም ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊዉ የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ክስ በማቅረብ መጠየቅ ይችላል(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1225/3 እና 1226 ይመለከቷል)። በዚህ መልኩ የንብረት መብት አድማስ ላይ ገደብ የሚጥለዉ ደንብ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149 ስር በንብረት ባለይዞታነት መብት ላይ የሚፈጠር ሁከት(ጣልቃ ገብነት) ለማስወገድ ከሚጠየቀዉ ዳኝነት የተለየ የንብረት ሕግ ጽንሰ ሀሳብ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

በተያዘዉ ጉዳይ ምንም እንኳን አመልካች በክሱ የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪ በሚሰራዉ የጋራዥ ሥራ የፈጸማቸዉ ተግባራት የሁከት ተግባራት ስለሆኑ ሊወገዱ ይገባል በማለት የጠየቁ ቢሆንም በተጠሪ በሚከናወነዉ የጋራዥ ሥራ ምክንያት የመኪና ቀለም ሲቀባ የሚወጣዉ ኬሚካል እና የመኪና አካል በሚሰራበት ወቅት የሚወጣዉ ከፍተኛ ድምፅ በሰላማዊ ሕይወታቸዉ እና በጤናችን ላይ ችግር እንደፈጠረባቸዉ የገለጹት የክስ ምክንያቶች ከላይ እንደተገለጸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1225 እና 1226 ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149 መሰረት በሌላ ሰዉ ይዞታ ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት(የሁከት ተግባር)የሚመለከት አይደለም።የስር ፍርድ ቤት ምንም እንኳን ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን የሕግ ድንጋጌ በመለየት በማስረጃ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ጋር በማዛመድ ዉሳኔ ያልሰጠ ቢሆንም የመኪና ቀለም ሲቀባ የሚወጣዉ ኬሚካል የሁከት ተግባር ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ድርሷል።ይህ ድርጊት የሁከት ተግባር ነዉ መባሉ ስህተት ቢሆንም ተጠሪ የንግድ ፈቃድ እንዳለዉና የጋራዥ ሥራዉንም የሚሰራዉ በሚመለከተዉ የመንግስት አካል በተፈቀደለት ቦታ ላይ ቢሆንም የመኪና ቀለም ሲቀባ የሚወጣዉ ሽታ ወይም ንዉጽዉጽታዎች(Nuisances) በጉርብትና አኗኗር አመልካች ሊታገሱት የማይችሉት ችግር ወይም ለጤና ጎጂ መሆኑን በማረጋገጥ ጉዳት እንዳይደርስ ተጠሪ አስፈላጊዉ የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሰጥቷል።

ምንም እንኳን አመልካች በቦታዉ ላይ ተጠሪ የጋራዥ ሥራ እንዳይሰራ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም በቦታዉ ላይ ተጠሪ የጋራዥ ሥራ መስራት እንደሚቻል በአካባቢዉ የልማት ፕላን መሰረት የሚመለከተዉ አስተዳደር አካል ፈቅዶለት እየሰራ እንደሚገኝ የስር ፍርድ ቤት የቀረቡለትን ማ[illegible]

CamScanner

ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ። በዚህ አግባብ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ላይ ሲደርስ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አኳያ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት ፈጽሟል ሊያስብል የሚችል ምክንያት አላገኘንም። በተጨማሪም አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የኦኪስጂን ጢስ እና መኪና ሲቀጠቀጥ የሚወጣዉ ብናኝ ወደ አመልካች ቤት ስለሚገባ በታማሚዉ ልጅ ላይ ዘላቂ ችግር እያስከተለ እንደሚገኝ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት በቸልታ አልፏል በማለት የገለጹ ቢሆንም በዚህ አግባብ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ የገለጹ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ አያሳይም።በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329/1 ስር እንደተደነገገዉ ለስር ፍርድ ቤት ያልቀረበዉን አዲስ ክርክር በሰበር ችሎት ደረጃ አቅርቦ መከራከር ስለማይቻል አመልካች በዚህ ረገድ ያነሱትን መከራከሪያ አልመረመርንም።

በአጠቃላይ ተጠሪ የጋራዥ ሥራ እየሰራ እንዲጠቀምበት በተሰጠዉ ቦታ ሲገለገል መቆቱን ያለመጠን በመገልገል ጎርቤቱ የሆኑትን አመልካች በሚጎዳ አኳኋን የሚፈጽመዉን የመኪና ቀለም መቀባት ሥራ እንዲያቆም የስር ፍርድ ቤት በማስረጃ በተረጋገጠዉ ልክ ዉሳኔ ሰጥቷል።ከዚህ ዉጭ ቦታዉ በአካባቢዉ ልማት ፕላን መሰረት ለጋራዥ ሥራ ሊዉል እንደሚችል ተረጋግጦ ተጠሪ የጋራዥ ሥራዉን እንዲሰራበት ቦታዉ በሚመለከተዉ የመንግስት አካል እንደተፈቀደለትና ከቀለም ቅብ ሥራ ዉጭ በጋራዡ የሚሰራዉ ሥራ የአመልካችን መብት እንዳልነካ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃ አረጋግጦ የሰጠዉ ዉሳኔ መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም አመልካች ሙሉ በሙሉ በቦታዉ ላይ የጋራዥ ሥራ እንዳይሰራ ሊወሰን ይገባል በማለት የጠየቁትን ዳኝነት የስር ፍርድ ቤት ዉድቅ በማድረጉ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት አልተፈጸመም።በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል።

ዉ ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 045603 ላይ በቀን 09/09/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36650 ላይ በቀን 14/10/2014ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 36839 ላይ በቀን 13/11/2014ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል።

1. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል።

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ። ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ።
2. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ጃኖች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

CamScanner